# መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ - መኢሶን -

# ALL ETHIOPIA SOCIALIST MOVEMENT (MEˊSONE)

## ቃለ መጠይቅ ከዶ/ር ነገደ ጎበዜ ጋር

### ያለፈውና መጪው ትግል

፩ኛ. የወቅቱ የፖለቲካ ሂደት

፪ኛ. ቀይ ሽብር

፫ኛ. መኢሶን፣ ሶቭየቶችና ኢትዮጵያ በ 1969

፬ኛ. መኢሶን ተሸንፏል ? ከኢሕአፓ በምን ይለያል ?

ለአንባቢዎች፤- ይህ ቃለ መጠይቅ ቀደም ሲል በጦቢያ መጽሄት በቅጽ 2 ከቁጥር 11 እስከ 12 1986፣ በቅጽ 3 ከቁጥር 1 እስከ 3 1986 በተከታታይ የወጣ ሲሆን፣ ብዙ በውጭ የሚገኙ አምስቱንም ቁጥሮች ተሟለተው ያላገኙ አንባቢዎች ድርጅታችንን በየጊዜው ከመጠየቃቸውም በላይ፣ በበኩላችንም ይህ የቃለ መጠይቅ ጽሑፍ ለአንዳንድ ጉዳዮች የውይይት መነሻ የሚሆኑ ነጥቦችን ያስጨብጣል ብለን ስለገመትን፣ ጽሁፉን አሰባስበን በዚህ መልክ አቅርበነዋል።

መልካም ንባብ

1987

